# Ethiopian Cultural Center in Belgium
# የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም

NEWSLETTER **ቁጥር 28 – July 18, 2021**

## ማውጫ Contents


**Brief History of Ethiopia – Part 18: The Era of Empress Zewditu (የእቴጌ ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት)**
The removal Lij Iyasu from the scene transformed a decade of political uncertainty in Ethiopian politics. It certainly initiated a period of considerable power struggle and ambiguity with the ruling class locked in an unfamiliar power structure. In the short term, the Shewan old nobility class were satisfied with the elimination of what they perceived as a looming political domination by Muslim-Oromo coalition and the ascendance to power, instead, of "one of their own".

**ገጽ 2-4**

---

**የስድተኛው ማስታወሻ (ክፍል 3)፤ ዳ.ሲ** መቼም ለስደተኝነት ወደ አውሮፓ ሲመጣ፤ ተይዞ የሚመጣው ምክኒያት እውነትም ይሁን ውሸት አሳማኝ መሆን ይኖርበታል። ምንም በጋዜጠኝነት ከጋዜጣ እስከ መፅሔት፤ ከመንግስት

**ገጽ 4-5**

---

**አጫጭር ወቅታዊ ዜናዎች Current News** የፌደራል ጠቅላይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ደ ክሮ በመጪው ማክሰኞ July 20 ባለፉት ቀናት በደረሰው የጎርፍ መጥለቅለቅ ጉዳት ለህልፈት ለተዳረጉ ዜጎች ብሄራዊ የሀዘን ቀን እንደሚሆን በጋዜጣዊ መግለጫቸው ላይ ተናግረዋል።

**ገጽ 5-6**

---

**ሳምንታዊ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት፤ በቤልጂየም** የኮሮና ቫይረስ ስርጭት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ቢሆንም ሆስፒታል መግባት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር ብዙም ለውጥ አላሳየም። የሟቾች ቁጥር ግን አሁንም እየቀነሰ ነው።በብዙ ቦታዎች በጣም ተላላፊ የሆነው የቫይረሱ የዴልታ ዝርያ ስርጭት ከፍተኛ እድገት እያሳየ ሲሆን ለምሳሌ በብራሰልስ ክልል በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በእጥፍ ጨምሯል። በቤልጂየም ውስጥ በ አጠቃላይ የዴልታ ዝርያ ሽፋን 65 በመቶ ይጠጋል።

**ገጽ 6-7**

**በኢትዮጵያ የኮቪድ 19 ስርጭት** **ገጽ 7-8**





website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

## Brief History of Ethiopia – Part 18: The Era of Empress Zewditu

The removal Lij Iyasu from the scene transformed a decade of political uncertainty in Ethiopian politics. It certainly initiated a period of considerable power struggle and ambiguity with the ruling class locked in an unfamiliar power structure. In the short term, the Shewan old nobility class were satisfied with the elimination of what they perceived as a looming political domination by Muslim-Oromo coalition and the ascendance to power, instead, of "one of their own".

On his part, Iyasu wanted to confront his adversaries with force and sent a small army to attack the Shewans in early October of that year. The army was met near Mieso and turned back, which led Iyasu to escape, according to some accounts, into the Ogaden desert. His father, Negus Mikael of Wollo, was displeased with his son's fate, then marched south from Dessie with about 80,000 troops in order to restore Iyasu to the throne. After initial skirmishes in Menz, the Battle of Segale, "one of Ethiopia's more important historic battles", opened in the early hours of 27 October 1916 and by noon Negus Mikael's army was defeated by a better prepared Imperial force led by the able general, Fitawrari Habte Giyorgis Dinagde. The army led by the deposed Lij Iyasu arrived too late to participate in the battle and fled back to Dessie together with his father's forces that escaped capture. He remained on the run until his was captured on 11 January 1921.

It is said that the bloodshed at the Battle of Segale was immense on both sides since the forces did not have distinctive dress or insignia, and the passwords, which were supposed to help, were not well known by everyone. It was the last organized attempt by Iyasu to reclaim his place at the helm. After this, in the words of Bahru Zewde, "(t)he coup was now sanctioned by blood". The battle also affirmed the dominance of the traditional nobility and curtailment of Lij Iyasu's foreign and domestic reform agenda. Even if it was almost purely an internal power struggle, this battle is thought of second only to the 1896 battle of Adwa to save Ethiopia's independence.

Zewditu was crowned on 11 February 1917, at a ceremony which European representatives officially attended for the first in Ethiopian history. Zewditu's official title was Negiste Negest ("Queen of Kings"), a modification of the male title of Niguse Negest ("King of Kings"). She was the first empress regnant of the Ethiopian Empire and the first female head of an internationally recognized country in Africa in the 19th and 20th centuries. She maintained her pledge to rule through her regent and didn't have active role in government business. Ras Tafari was the most visible face of her government even at public occasions. However, she wasn't a passive, "honorary ruler" but rather took part in the decision-making processes, usually having the last word which everyone, including the regent, had to live by.




website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

Ras Tafari Makonnen, as an heir to the throne, was supposed to have a very influential place national politics. However, his position was politically, militarily and financially too weak to have a meaningful leverage on the more powerful empress and, more importantly, the minster of war, Fitawrari Habte Giyorgis.

Even then, Tafari began to introduce a degree of modernization into Ethiopia in the early 1920s. He introduced administrative regulations and appointed ministers to advise him. He also ensured the growth of educated class (potential allies), by promoting government schooling first by expanding the school Menelik had established and founding the Tafari Mekonnen Elementary School in 1925. Tafari also acted to extend his power base abroad by attempting to get Ethiopia into the League of Nations. The first attempt failed in 1919 because of the existence of slavery. In consultation with Empress Zewditu, he managed to ban the slave trade in 1923, which allowed Ethiopia to gain a membership of the League of Nations the same year by unanimously vote.

Joining the League of Nations was motivated in part by the desire ensure that Ethiopia benefits from the League's promise of collective security. Ras Tafari believed that membership in the League of Nations would protect Ethiopia from external threat and the intrigues of the great powers. He was also convinced that the survival of Ethiopia's independence required her to modernize by opening herself to the world. But these internationalization efforts of the Ras were not immediately popular in Ethiopia. That the Empress (a religious conservative and a believer in preservation of Ethiopian tradition) finally sided with Tafari for an open Ethiopia as opposed to Fitawrari Habte Giorgis, "who deeply abhorred foreign connections and who believed in Fortress Ethiopia" helped him grow in political stature.

The death of Habte Giorgis in December 1926 dramatically changed the political landscape in the country and enabled Ras Tafari to take effective control of the government, with no overt attempt to thwart his reforms. He all but ignored the ideas of the apathetic Empress in his decisions.

Frustrated at Empress' declining relevance in the running of the government, a small group of supporters and palace reactionaries attempted an unsuccessful coup d'état in September 1928 in a bid to get rid of Ras Tafari. In the aftermath, Empress Zewditu was compelled to grant Ras Tafari the title of Nigus (King). Thereafter, a number of unsuccessful attempts including a rebellion in Begemdir led by Ras Gugsa Welle, Zewditu's husband, were made to remove Negus Tafari who was now in effect the ruler of Ethiopia. Ras Gugsa, acting apparently against the will of his wife, was defeated and killed at the Battle of Anchem on 31 March 1930. This battle was probably the first time an aircraft equipped with bombs was used by




website https://www.ethiopianculturalcenter.be/

Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com

facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

Ethiopian army. It was piloted by a Frenchman and marked the birth of the Imperial Ethiopian Air Force.

By coincidence of fate or otherwise, Empress Zewditu died on 2 April 1930, just two days after Ras Gugsa Welle was killed in battle. Although it is known today that she suffered from diabetes, liver complications and was seriously ill with typhoid, the accounts of the immediate cause of her death remained unclear.

Immediately after her funeral the same night in Menelik's mausoleum, the crown council proclaimed Negus Tafari emperor and he succeeded to the throne unopposed. The succession struggle thus ended in favor of Tafari, seventeen years after the official death of Emperor Menelik II. ... *to be continued*

==========================================================================

**የስደተኛው ማስታወሻ - ክፍል 3 ዳ.ሲ**

መቼም ለስደተኝነት ወደ አውሮፓ ሲመጣ፤ ተይዞ የሚመጣው ምክኒያት እውነትም ይሁን ውሸት አሳማኝ መሆን ይኖርበታል። ምንም በጋዜጠኝነት ከጋዜጣ እስከ መፅሔት፤ ከመንግስት ቴሌቪዥን እስከ ግል የተለያዩ ሬዲዮ ጣቢያ ውስጥ መስራቴ ነገሮችን ለማቀናጀት ባይከብደኝም የቤልጅየም ስደተኛ ቢሮ የሚፈልገው አቀራረብ ምን መሆን አለበት የሚለውን በተመለከተ ግን ወደ ስድስት የሚሆኑ ምክክሮችን ስምንት ከሚሆኑ ልበ ቀና ወዳጆቼ ጋር አድርጌያለሁ። ለእኔ የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት ይገኙ የመጣሁት እውነት ብቻ ሳይሆን የወዳጆቼ መልካም ጥረት የጉዳዬን ቅርፅና ይዘት የመወሰን ጉልበት ሁሉ ነበረው። ከሁለት ሳምንት አስቸጋሪ የስምንት ሰው ኑሮ በኋላ አሁን ወደ 'ደረጃ አንድ' የመኖሪያ ክፍል ተዛወርኩ። ከእንጨት፣ ሞቃት፣ ሙላተ ጭስና እንቅልፍ አልባ ክፍል ወደ አራት ሰው፣ ብሎኬት፣ ንፁህና ሰላማዊ ክፍል ተዛወርኩ። ሁለት ኤርትራዊ፣አንድ ሶማሌያዊና አንድ ኢትዮጵያዊ እዚህ ክፍል አለን።

እዚህ ክፍል የተዘዋወርኩ ቀን ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ላይ የምንኖርበት ኮሪደር በጩኸትና ግርግር ተሞላ። በዚህ ኮሪደር ላይ በቀኝና በግራ ስድስት ስድስት የሚሆኑ ክፍሎች አሉ። ከኢራቅ፣ አፍጋኒስታን፣ ሶሪያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ሩሲያ፣ ቺቺኒያ፣ሊቢያ ከስምንት መቶ ስደተኛ አንድ ኢትዮጵያዊ እንገኛለን። ጩኸቱን ሰምቼ ወዲያው አልወጣኹም። ምክኒያቱ ደግሞ ከዚህ በፊት እንደሰማኹት ጉዳዩ የቡድን ይሆንና የተገኘው ሁሉ የቢላ ሰለባ ይሆናል። ከደቂቃዎች በኋላ ስወጣ አንድ ኢራቅ በአንድ አፍጋኒስታዊ በቀኝ ኩላሊቱ በኩል ተወግቶ ደሙ እየፈሰሰ ወድቆ ድብድቡና ጩኸቱ በርክቶ ከሌሎች ኮሪደሮች የነበሩ ሁሉ ተጠራርተው ኮሪደሩ የጦርነት ከውድማ መስሏል። በበራችን አጮልቀን እናይ የነበርን ሁሉ ተመልሰን በራችንን ዘግተን የሚሆነውን መጠበቅ ጀመርን። የፖሊስ ሳይረን የሚያሰሙ መኪኖች ካምፓችንን እየቀረቡ መጡ። የፓሊሶቹን ድምፅ በኮሪደራችን ላይ ስንሰማ እየተረጋጋን ወጣን። ሁለት ሚኒ ባስ፣ አራት ትንንሽ መኪና ሙሉ ፖሊስ፤ አምቡላንስና ሌሎችም የእርዳታ ሰጪ ሰራተኞች ካምፓችንን ወረሩት። ሁላችንም ልብሳችንን እያጠለቅን ወደ ጊቢው ወጣን። ከሌሊቱ ዘጠኝ (03:00 እኤአ) ሰዓት ይሆናል።

ከሁለት ሰዓት በኋላ ልብሴን ለባብሼ የሁለት ሰዓት ተኩል የባቡር ጉዞ ወደ ብራስልስ አድርጌ ሁለተኛውንና ወሳኙን ቃለ ምልልስ ማድረግ ይኖርብኛል። በአንድ በኩል እንቅልፍ በሌላ በኩል ደግሞ በግቢያችን ውስጥ አሁን የማየው ሁሉ ፊልም መሰለኝ። ይህን ሁሉ አልፌ የመኖሬያ ፍቃድ ማግኘት የግድ ነው። ለቁርስ ዳቦ ማርማራት በምንቀባበት ቢላ የተወጋው ተጎጂ አምቡላንስ ውስጥ ህክምና እየተሰጠው ሔዱ። ፖሊሰዎቹ በግርግሩ ውስጥ ተሳተፉ ያሏቸውን ሰብስበው ወጡ። የተወሰኑት በጊቢው ቀርተው ሰዎችን መጠየቅና ማረጋጋት እንዲሁም ከቀይ መስቀል ኃላፊዎች ጋር እየተነጋገሩ አየን። እኔም ወደ ክፍሌ



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

ተመልሼ የቀረኝን አንድ ሰዓት ጊዜ ጉዳዬን የፃፍኩበትንማስታወሻ አውጥቼ መገረቤን ቀጠልኩ። ይቀጥላል..

=====================================================================================

## አጫጭር ወቅታዊ ዜናዎች

**በቅርቡ በደረሰው የጎርፍ አደጋ ያደረሰው ጉዳት አሳሳቢ ሆኗል።**

የሰሞኑ የአየር ሁኔታ ከፍተኛ የንብረት ጥፋት ከማድረሱ በተጨማሪ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በጎርፉ ምንክያት 27 ሰዎች ህይወታቸውን ያጡ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን 103 ሰዎች ጠፍተዋል ወይም ሊደረስባቸው አልተቻለም። እንደ የአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል (Crisis Center) ገለጻ ሰዎች አልተገኙም ማለት ሞተዋል ማለት ባይሆንም የሟቾች ቁጥር ግን ሊጨምር ይችላል ተብሎ ይጠበቃል። የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶች በአካባቢው በሙሉ ፍለጋ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። ቤልጂየም እስካሁን ካየቻቸው እጅግ አስከፊ አደጋዎች ሁሉ በላይ ይሆናል የተባለው የጎርፍ መጥለቅለቅ እስከ 5 አገራት አዳርሷል። አራት የዕርዳታ ሰጪዎችን ጨምሮ በጀርመን በደረሰ የጎርፍ አደጋ ቢያንስ 156 ሰዎች መሞታቸው ታውቋል። ወደ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን ብዙዎች የት እንደደርሱ ስለማይታወቅ የሟቾች ቁጥር የበለጠ ሊጨምር ይችላል።

**በጎርፍ ለደረሰው ጉዳት ለJuly 20 ብሔራዊ የሀዘን ቀን ታወጀ።**

የፌደራል ጠቅላይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ደ ክሮ በመጪው ማክሰኞ July 20 ባለፉት ቀናት በደረሰው የጎርፍ መጥለቅለቅ ጉዳት ለህልፈት ለተዳረጉ ዜጎች ብሄራዊ የሀዘን ቀን እንደሚሆን በጋዜጣዊ መግለጫቸው ላይ ተናግረዋል። በዚሁ ቀን የአንድ ደቂቃ ዝምታ ይደረጋል። ረቡዕ July 21 የሚከበረው የቤልጂየም ብሔራዊ ቀን በዚሁ ምክንያት ከተጠበቀው መጠን የተቀዛቀዘ ይሆናል። ይህም ለሟቾች ክብር ብቻ ሳይሆን ብዙ ወታደሮች የተጎዳውን አካባቢ ነዋሪዎች እየረዱ ስለሆኑ ለወታደራዊ ሰልፍ ሊገኙ ስለማይችሉ ነው።

**ቤልጂየም ከተለያዩ አገራት የመጡ ከ250 በላይ የነፍስ አድን ሠራተኞች እርዳታ አግኝታለች።**

በቅርቡ የደረሰውን የጎርፍ አደጋ ለመቋቋም እና ለተጎጂዎች ለመድረስ ከውጭ እርዳታ ድጋፍ ስለተፈለገ ከ250 በላይ እንደ ፈረንሣይ፣ ኦስትሪያ፣ ጣሊያን፣ ጀርመን፣ ኔዘርላንድስ እና ሉክሰምበርግ ካሉ አገራት የመጡ የነፍስ አድን ሠራተኞች ደርሰዋል። የነፍስ አድን ሠራተኞቹ የመጡት የቤልጂየም የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር አነሊስ ቬርሊንደን የአውሮፓን ሲቪል መከላከያ ትብብርን በደንቡ መሰረት አለም አቀፍ ድጋፍን ስለጠየቁ ነው። የነፍስ አድን ቡድኖቹ ልዩ ልዩ ባለሙያተኞችን ያሉበት ሲሆን ጀልባዎች፣ ሄሊኮፕተሮች፣ ድሮኖች እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችንም ይዘዋል። ዕርዳታውን የሚያስተባብረው የአውሮፓ ኮሚሽን እንደሆነ ታውቋል።



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

# Ethiopian Cultural Center in Belgium
# የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም

**ትክክለኛ የኮሮና ሰነዶች ሳይዙ ለሚጓዙ ቅጣት ተዘጋጅቷል።**

ትክክለኛ ያልሆነ ከኮሮና ጋር የተያያዘ ሰነድ በመያዝ ከቤልጂየም ለመውጣት ወይም ወደ ቤልጂየም ለመምጣት የሚሞክሩ ማናቸውም ተጓዦች 250 ዩሮ ቅጣት ይጣልባቸዋል። ሰነዱ የተጭበረበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እስከ 750 ዩሮ ቅጣት ይጠበቃል። ዕድሜያቸው ከ6 ዓመት በላይ የሆኑ ተጓዦች ጉዟቸውን ከመጀመራቸው በፊት የአውሮፓ ዲጂታል ኮሮናና ሰርተፊኬታቸውን (European Digital Corona Certificate) መያዝ እንዲሁም የተሳፋሪ ማግኛ ቅጽ (Passenger Locator Form) በትክክል መሙላት አለባቸው። ወደ ቤልጂየም የሚበሩ ተጓዦች በሙሉ የተሳፋሪ ማግኛ ቅጹን በትክክል ካልሞሉ እንዲሳፈሩ መፈቀድ የለበትም። ዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ ለቫይረሱ እና ወረርሽኙ ስርጭት ዓይነተኛ መንገድ በመሆኑ ቁጥጥሩ መጥበቅ እንዳለበት ታምኗል።

በተያያዘ ዜና አንድ ተሳፋሪ በብራስልስ አውሮፕላን ማረፊያ የሐሰት የPCR የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ውጤትን በማቅረቡ በአንድ ዓመት እስራት ተቀጣ። ግለሰቡ ለአጭበርባሪዎች 30 ዩሮ መክፈሉን ያመነ ቢሆንም በቦታው 750 ዩሮ እንዲከፍል ሲጠየቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ ክስ ከተመሰረተበት በኋላ የአንድ ዓመት እስራት እና የ4000 ዩሮ ክፍያ ተፈርዶበታል።

========= ===== ===== ===== ========== ======= ==========

**ቤልጅየም - ሳምንታዊ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት፤**

በቤልጂየም የኮሮና ቫይረስ ስርጭት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ቢሆንም ሆስፒታል መግባት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር ብዙም ለውጥ አላሳየም። የሚኞች ቁጥር ግን አሁንም እየቀነሰ ነው። በብዙ ቦታዎች በጣም ተላላፊ የሆነው የቫይረሱ የዴልታ ዝርያ ስርጭት ከፍተኛ እድገት እያሳየ ሲሆን ለምሳሌ በብራሰልስ ክልል በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በእጥፍ ጨምሯል። በቤልጂየም ውስጥ በ አጠቃላይ የዴልታ ዝርያ ሽፋን 65 በመቶ ይጠጋል።(ምንጭ: የማህበረሰብ ጤና ሳይንስ ተቋም - Sciensano)

በቤልጅየም የማህበራዊ ጤና ሳይንስ ተቋም በሳምንቱ መጨረሻ የዘገበው መረጃ የሚከተለው ነው።

- ከJuly 7 እስከ 13 ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ በየቀኑ በአማካይ **1,231** ሰዎች በኮሮና ቫይረስ እንደተያዙ ታውቋል። ይህ ከሳምንት በፊት ካለው አሃዝ ጋር ሲነጻጸር **በ76 በመቶ** መጨመሩን ያሳያል። በዚህም መሠረት ወረርሽኙ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በምንኖርባት አገራችን በአጠቃላይ **1,103,413** ሰዎች በቫይረሱ መያዛቸው ተረጋግጧል።
- በአጠቃላይ በአሁን ሰዓት **239** የኮቪድ-19 ህመምተኞች በተለያዩ ሆስፒታሎች ውስጥ በህክምና እየተረዱ ይገኛሉ። ይህ ቁጥር ከባለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር ምንም ለውጥ አላሳየም።
- በየሆስፒታሎቹ ካሉት የኮቪድ-19 ህመምተኞች ውስጥ **81** ታማሚዎች በጽኑ ሕሙማን ክፍል በከፍተኛ እንክብካቤ ላይ ይገኛሉ። ከባለፈው ሳምንት አንጻር ሲታይ ወደዚህ ክፍል መግባት ያለባቸው ህመምተኞች ቁጥር **በ13 በመቶ** ቀንሷል። ከጽኑ ህሙማን ውስጥ ሰው ሰራሽ የመተንፈሻ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር **50** ሲሆን ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር **በ24 በመቶ** ቀንሷል።
- **ሆስፒታል የሚገቡ:** ከJuly 10 እስከ 16 ድረስ በየቀኑ በአማካይ **21** ሰዎች በኮቪድ-19 ምክንያት ሆስፒታል ገብተዋል። ይህ ቁጥር ካለፈው ሳምንት ጋር ሲነጻጸር **በ21 በመቶ** ጨምሯል።
- **የሚኞች ቁጥር:** ከJuly 7 እስከ 13 በነበረው ሳምንት በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በየቀኑ በአማካይ **2** ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል። ይህ ቁጥር ከባለፈው ሳምንት ጋር

ሲነጻጸር **በ42 በመቶ** ቀንሷል። በዚህ መሰረት በምንኖርባት አገራችን አጠቃላይ የሚቾች ቁጥር **25,209** ደርሷል።

- እስከ July 15 ድረስ በቤልጅየም ውስጥ **7,706,816** ሰዎች ቢያንስ የመጀመርያውን ክትባት ወስደዋል። ይህ **82 በመቶ** የሚሆነው የጎልማሳ ህዝብ ቁጥር ነው። ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጨምሮ ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ ደግሞ ይህ ወደ **66.9** በመቶ ይደርሳል። ከእነዚህ ውስጥ **5,292,222** ሰዎች ሁለተኛውንም ክትባት ስለወሰዱ ሙሉ በሙሉ ተከትበዋል ማለት ነው።

**ማጠቃለያ (እስከ July 16, 2021)**

| የሰው ቁጥር | በጠቅላላ | ባለፉት 7 ቀናት (በየቀኑ አማካይ) | ባለፉት 14 ቀናት (በየቀኑ አማካይ) |
|---|---|---|---|
| የህመምተኞች | 1.1 ሚሊዮን | 1,231 (+76%) | 966 (+155%) |
| የሚቾች | 25,200 | 2 (-42%) | 2 (-55%) |
| ሆስፒታል የገቡ | 75,700 | 21 (+21%) | 19 (-9%) |
| ምርመራ የተደረገላቸው | 16.3 ሚሊዮን | 63,200 (+0%) | 63,200 (+47%) |
| አንድ ጊዜ የተከተቡ (>18 ዓመት) | 7.7 ሚሊዮን | 26,600 (-46%) | 37,900 (+16%) |

**ተያያዥ ዜና፥ የምክክር ኮሚቴ ነገ ይካሄዳል**

ነገ ስለ ኮሮና ሁኔታ የምክር ኮሚቴ ስብሰባ ይኖራል። የተለያዩ የሀገሪቱ መንግስታት ተወካዮች ያሉበት ኮሚቴ በመደበኛነት አርብ ዕለት መሰብሰብ ሲኖርበት የጎርፉ አደጋ ባመጣው አስቸጋሪ ሁኔታ ምክንያት ስብሰባው ተላልፏል።

የቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ለተከታታይ ቀናት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ቢሆንም አዲስ እግድ ወይንም ያሉትን እግዶች የሚያጠናክር ውሳኔ አይጠበቅም። በዋናነት የሚወያዩበት አጀንዳ ተጓዦች ላይ ስለሚደረጉት ጥብቅ ቁጥጥሮች፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች የክትባት አስገዳጅነት ያስፈልጋል ወይ እና ሀገር ውስጥ ለሚደረጉት ህዝብ የሚሰበሰብባቸው መለስተኛ ዝግጅቶች ላይ የኮሮና ይለፍ ማስረጃ (Corona Pass) አስፈላጊነትን ያካትታል።

---

**በኢትዮጵያ የኮቪድ 19 ስርጭት**





website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium

# Ethiopian Cultural Center in Belgium
# የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም

በ 12/07/2021 በተደረገ 4,358 የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራ 66 ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ እስካሁን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 277,137 ደርሷል። በሌላ በኩል 33 ሰዎች ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ 262,022 ሰዎች ከበሽታው አገግመዋል።




በ 17/07/2021 በተደረገ 4,645 የላቦራቶሪ ናሙና ምርመራ 79 ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ እስካሁን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 277,615 ደርሷል። በሌላ በኩል 28 ሰዎች ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ 262,265 ሰዎች ከበሽታው አገግመዋል።

ውድ አንባቢያን ከላይ እንደምትመለከቱት የኮቪድ 19 ስርጭትን የሚያሳዩት የመረጃ ሰንጠረዥ እንደሚገልጹት በቫይረሱ የሚያዙት ሰዎች መጠን ዝቅተኛ ቢሆንም ሁሌም እንደምንለው ጥንቃቄ አይለየን።

መልካም ሳምንት መልካም ንባብ



website https://www.ethiopianculturalcenter.be/
Email ;ethioculturalcenterbelgium@gmail.com
facebook: የኢትዮጵያ ባህል ማእከል በቤልጅየም/ Ethiopian Cultural Center in Belgium